African Population and Health Research Center | IDRC | CRDI International Development Research Centre / Centre de recherches pour le développement international | Canada | Global South AI4COVID Program

# የሥርዓተ-ጾታና ብዝሃነት በሰአ ማመሳከሪያ የክትትልና የመማማሪያ ቅጽ

**ኦክቶበር 2022**

## መግቢያ

ጥበብ በጎደለው መንገድ ጥቅም ላይ ከዋለ ሰውሰራሽ አስተውሎት (ሰአ) (Artificial Intelligence) በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ ያሉ የተዛቡና ጭፍን አመለካከቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህንን ችግርለመከላከል የአፍሪካ የህዝብና ጤና ምርምር ተkም (African Population and Health Research Center (APHRC)) "የሥርዓተ-ጾታና ብዝሃነት በሰአ" የተሰኘ ማመሳከሪያ ቅጽ (Checklist) አቀናብሮ አቅርባል። የተቀረጸው የማመሳከሪያ ቅጽ በሰአ ዙሪያ ያለውን የሥርዓተ-ፆታ ነክ የመረጃ ክፍተት በተቻለ መጠን ለመድረስ የታለመ ሲሆን፤ ይሕ የክትትልና የመማሪያ ቅጽ ደግሞ በሰአ ዙሪያ የሚደረጉ የስርዓተ-ፆታና የብዝሃነት አካታችነት ጥረቶች በጤናው ዘርፍ በምን መልኩ የተሸለ ውጤቶች እንዳስገኙ ለመከታለል የሚያስችል ነው። ይህ የክትትልና የመማሪያ ቅጽ ግለሰቦች፣ ለጋሾች፣ መንግስታት፣ የምርምር ተkማት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተkማትና የመሳሰሉት የስርዓተ-ፆታና ብዝሃነት ጉዳዮችን በሰአ ስልተ-ቀመራቸው (algorithm) ላይ በቼክሊሰቱ መሠረት ማከተታቸውን እንዲሁም በማካተታቸው የተገኙትን ውጤቶች ለመገምገምና ከጥረታቸውም ትምህርት ለመቅሰም የተቀረጸ ነው።

ይህ የመከታተያና መማማሪያ ቅጽ ሲቀረጽ የሚከተሉትን ዋና ዋና ዓላማዎች ታሳቢነት በማድረግ ነው።

ሀ. በትልም/ዲዛይን፣ በመረጃ የማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማሰራጨት ወቅት የማመሳከሪያ ቅጹ በምን ያክል ሁኔታ እንደተተገበረ ስለታዊ በሆነ መንገድ ለመከታተል፣

ለ. የሥርዓተ-ፆታና የብዝሃነት መረጃዎች በሰአ ስልተ-ቀመር ውስጥ ከጅምሩ በመካተታቸው በምርምር ውጤቱ ላይ ያስገኘውን ውጤት ለመከታተል።

በተጨማሪም ይህ የመከታተያና የመማሪያ ቅጽ

- የሥርዓተ-ፆታና የብዝሃነት መረጃዎችን ያካተተ ሰአ ምርምር ሥራዎችን አፈጻጸም ለመከታተል
- በሰአ ምርምሮች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታና የብዝሃነት መረጃዎችን በመካተታቸው የተገኙ ትምህርት/ተሞክሮዎችን (ክፍተቶችን ጨምሮ) አንጥሮ ለማውጣት
- የተገኘው መረጃ ምን ያክል በሥራ ላይ መዋል የሚችል መሆኑን ለመረዳትና ከተሞክሮዎቹ የምንወስዳቸውን ትምህርቶች ለመመርመር

ይረዳል ተብሎ ይታመናል ።

## አካሄድ

ይህ የመከታተያና የመማሪያ ቅጽ "የሥርዓተ-ጾታና ብዝሃነት በሰአ ማመሳከሪያ ቅጽ" ዋነኛ አካል ነው። መመርመር/መከታተል ያለብንን ቁም ነገሮች የውጤት አመላካች ጠkሚዎችን (indicators) በመጠቀም ማመሳከሪያው በሰአ ስልተ-ቀመር ውስጥ ያለውን የሥርአተ-ፆታና የብዝሃነት ክፍተት በምን ሁኔታ ለማጥበብ ጠቅማዕል የሚለውን ጥያቄ በተከታታይነት ለመገምገም እንዲመች እድል ይፈጥራል። የውጤት አመላካች ጠቀôሚዎች የስርዓተ-ፆታና የብዝሃነት ጉዳዮች በምርምር ሥራዎችና ውጤታቸው ላይ መካተታቸውንና ውጤቱንም ማሳያ በመሆን ያገለግላሉ። ይህንን የመከታተያና የመማሪያ ቅጽ በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ይመከራል።

- የመረጃ/ዳታ ማሰበሰሰቢያ መንገዶችዎን ትልም አዘጋጅተውና የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓቱን ከመጀመርዎ በፊት በማመሳከሪያ ቅጹ ላይ የተመለከቱት ጥያቄዎች በሚገባ መካተታቸውን ያረጋገጡ። እዚህ ላይ ትልምዎ በተቻለ መጠን በበቂ ሁኔታ በሥርዓተ-ፆታና ብዝሃነት ጉዳዮች ዙሪያ ጥራትንና ብዛትን

(qualitative and quantitative data) የሚያመላክቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑን ያረጋግጡ፣

- መረጃ በማሰባሰብ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ውስጥ ናሙና በመውሰድ የመረጃዎቹን ሁኔታ ማጥናትና የሥርዓተ-ፆታና የብዝሃነት ጉዳዮች በበቂ ሁኔታ እያሳየ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ካልሆነም ተግዳሮቶችን በመለየትና ከተወሰዱት ትምህርቶች በመነሳት አስፈላጊውን ማስተካከያ እርምጃዎች ከወዲሁ መውሰድ፣
- መረጃው በሚተነተንበትም ወቅት የሥርዓተ-ፆታና የብዝሃነት ጉዳዮች በተለይም በተለምዶ በቀላሉ የሚገለሉ የማህበረሰብ አባላትን ጉዳዮች የተሰበሰበው መረጃ በሚገባ የማሳየቱን ያረጋግጡ፡፡ ብሎም ትንተናው ግለጽ የሆነ እዲሁም ከተጨባጭ መረጃ ላይ ተነስቶ በተግባር መዋል የሚችል መደምደሚያና ምክረ ሃሳብ ማካተቱን ያረጋግጡ፣
- የተገኙ ውጤቶችን/ለውጦችን ሲለኩ (ወይም ውጤት አልባነቱን አልያም ያልታሰቡ ውጤቶችን ) ሲዘግቡ በያንዳንዱ አመላካች ጠቀዕሚ ሃሳቦች ስር የማያከራክር ግልጽ ማስረጃ መሰብሰቡንና በተቻለ መጠን በቂ ምሳሌዎችን መሰበሰቡን ያረጋግጡ፣
- አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ያልተገመቱ/ያልታሰቡ ውጤቶችን ወይም ምንም ውጤት አለመገኘቱን መገንዘብ ከተሞክሮዎቻችን ለማማር አስፈላጊ ሂደቶች በመሆናቸው እነዚህን ሁኔታዎች ቸል ማለት አያስፈልግም፣
- በክትትል ሲያደርጉ በአመላካች ነጥቦች ላይ በቂ መረጃና ምሳሌዎችን ወይም የማረጋገጫ ሃሳቦችን ማግኘትዎን ሳያረጋግጡ በፊት ምንም ዓይነት ድምዳሜዎችንም ሆነ ምክረ ሃሳቦች ላይ ከመድረስ ይታቀቡ፣
- በመጨረሻም መደምደሚያዎችና የምንሰጣቸው ምክረ ሃሳቦች የሥርዓተ-ፃታንና የብዝሃነትን ጉዳዮች በሚገባ ያካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡




## የዚህ ክትትልና መማማሪያ ሂደት የማስፈጸም ሃላፊነት ያለበት አካል ማነው?

- የመንግስት፣ የለጋሾች፣ የምርምር ተቀዕማትን፣ የሥነምግባር ቦርድ እዲሁም የሥርዓተ-ፆታ መረጃ መረቦችን ፖሊሲ እቅጣጫ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ማንኛውም ሰአን ለማሕበረሰባዊ ለውጥና ፒሊሲ ጥቅም ላይ ማዋል የሚፈልግ አካል
- እንዲሁም የሥርዓተ-ፆታና የብዝሃነት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩና በጉዳዮቹም ዙሪያ ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚተጉ ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት

## በክትትል ወቅት መታየት ያለባቸው ዋና ጉዳዮች

### 1. የመረጃው የአካታችነት ሁኔታ



መታየት ያለባቸው ቁልፍ ማመላከቻዎች

- የሥርዓተ-ፆታና ብዝሃነት ጉዳዮችበሰአ ስልተ-ቀመሮች ላይ በምን ሁኔታ ተካተዋል
  -በበቂ ሁኔታ
  -በመጠነኛ ሁኔታ
  -ምንም አልተካተተም

እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

- ሊያጋጥሙ የሚችሉ አዳጋች ሁኔታዎች ከወዲሁ የተካተቱበት/የተተነበዩበት ሁኔታ (ለምሳሌ የመረጃ ክፍተቶችና በመረጃዎች ዙሪያ ሊኖሩ የሚችሉ የተዛቡ አመለካከቶችን ከወዲሁ ግምት ውስጥ መካተት)
  -በበቂ ሁኔታ
  -በመጠነኛ ሁኔታ
  -ምንም አልተካተተም

እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

- የመረጃ ማሰባሰቢያው ሂደት የሥርዓተ-ፆታና ብዝሃነት ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን በምን መልኩ ለመሙላት ያስችላል
  -በበቂ ሁኔታ
  -በመጠነኛ ሁኔታ
  -ምንም አያስችልም

እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

- የመረጃ ማሰባሰቡ ሂደት የተለያዩና የሚመጋገቡ ( መረጃን በጥራትና በብዛት ለማሰባሰብ የሚስችሉ) የመረጃ ምንጮችን የማካተት ሁኔታ
  -በበቂ ሁኔታ
  -በመጠነኛ ሁኔታ
  -ምንም አልተካተተም



እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

### 2. ህጋዊነትን ማረጋገጥ

መታየት ያለባቸው ቁልፍ ማመላከቻዎች

- በሥርዓተ-ፆታና በመረጃ ግለዊነት (privacy) ዙሪያ ያሉ መመሪያዎችንና ፖሊሲዎችን ከግምት ውስጥ የማስገባት ሁኔታ (ምሳሌ ይስጡ)
  -በበቂ ሁኔታ
  -በመጠነኛ ሁኔታ
  -ምንም አልተካተተም
- የሰአ ሥርዓቱ ( AI system) ምን ያህል አስተማማኝነት ነው?[1]

### 3. የአሰራር ሥርዓትና ሂደቶች

መታየት ያለባቸው ቁልፍ ማመላከቻዎች

- ትንበያዎች በስርዓተ-ፆታና በብዝሃነት ዙሪያ ያሉ ልዩነቶችንና ተሞክሮዎች ምን ያክል ያንጸባርቃሉ? ምሳሌዎችን ጥቀስ
  -በበቂ ሁኔታ
  -በመጠነኛ ሁኔታ

[1] Berryhill, A. and Fuentes, L. Technical Brief 1: Designing gender-responsive data projects. Ladysmith2. Available at: https://covidsouth.ai/research/download/English-Technical-Brief-1-Designing-gender-responsive-data-projects

-ምንም አያንጸባርቁም

እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

- ተገቢውን መንገድ በመጠቀም የሰአ ሞዴሎችና መረጃዎች ከተዛባ አመለካከት የጸዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሁኔታ

-በበቂ ሁኔታ

-መጠነኛ ሁኔታ

-ምንም አያረጋግጥም

እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

- የሥነምግባርና የፍትሃዊነት ስጋቶችን ለመፍታት የሚያስችል የተጠያቂነት አሰራር አለ

-በበቂ ሁኔታ

-በመጠነኛ ሁኔታ

-ምንም የለም

እባክዎ የምርጫዎን ትክክነኛነት ለማረጋገጥ የሚረዳ በቂ ማስረጃዎች ያመላክቱ

## 4.ትምህርት መውሰድ

## መደምደሚያና ምክረ-ሃሳቦች

በየአንዳንዱ ቁልፍ የለውጥ አመላካቾት/ጠቀôሚዎች ዙሪያ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ቀጣዩ ሥራችን በተደጋጋሚ እየመጡ ያሉ ሃሳቦችን፣ መነሳት ያለባቸውን ጥያቄዎችን፣ ቀጣይ አካሄዶችንየመለያ ሥራዎችን መሥራት ይሆናል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በተቻለ መጠን አንድ በአንድ ከመመለስዎ በፊት ማንኛውንም መደምደሚያም ሆነ ምክረ ሃሳቦችን ከመስጠት እንዲቆጠቡ ይመከራል፡፡

- በእጃችን ካለው መረጃ ላይ በመመርኮዝ ምን አይነት ተደጋጋሚ ሃሳቦችን እየተመለከትን ነው?
- ምን ምን ጥያቄዎች እየመጡ ነው/ማለትም የበለጠ መመርመር ያለባቸው ጉዳችን ምንድን ናቸው ?
- ከነዚህ ተደጋጋሚ ሃሳቦች ምን ትምህርቶችን መውሰድ ወይም ጥያቄዎች መነሳት ይችላሉ?
- ከዚህ መረጃ በመነሳት ምን አይነት መደምደሚያዎች ላይ መድረስ እንችላለን?
- እነዚህ መደምደሚያዎችን ለመተግበር ምን አይነት ቀጣይ እርምጃዎች መውሰድ ይቻላል?

በተጨማሪም መደምደሚችንና ምክረ ሃሳቦችን ከማጠናቀቃችን በፊት ከታች የተዘረዘሩትን አራት ጥያቄዎች[2] መመልከት በመረጃ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ የተዛቡ አመለካከቶችንና ለአደጋ የሚያጋልጡ ውጤቶችን ለመቀነስ ይረዳሉ፡፡

- መረጃው ምን ያህል አካታች ነው ?
- የመረጃ ሞዴሉ የተዛቡ አመለካከቶችን በምን መልኩ ይመለከታቸዋል?
- ትንበያዎቹ ከbigdata አንጻር ሲታዩ ምን ያክል ትክክለኛ ናቸው?
- Big data ላይ መመርኮዛችን የስነምግባርና የፍትሃዊነት ጥያቄን ያስነሳብን ይሆን?

[2] Big Data: A Tool for Inclusion or Exclusion? Understanding the Issues (FTC Report). Available at: https://www.ftc.gov/reports/big-data-tool-inclusion-or-exclusion-understanding-issues-ftc-report